ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
Forum for Social Studies(FSS)

ህዳር 2013 | የፖሊሲ ፍሬ ኃሳቦች | ቁጥር 44

# አርብቶ አደርነት የመሬት አጠቃቀምና መብት በኢትዮጵያ

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ ነክ ምርምሮችን የሚያካሂድ ለትርፍ ያልተቋቋመ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው፡፡

♣ ♣ ♣

የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፤ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፤ የተለያዩ የሕብረተሠብ ክፍሎችን ጋብዞ ያወያያል፡፡

♣ ♣ ♣

በድረ-ገጹ የሕትመት ውጤቶቹን ዝርዝር ያቀርባል፤ በልማት ዙሪያ ውይይቶችንም ያካሂዳል፡፡

♣ ♣ ♣

በርዕሱ ዙሪያ ኃሳብ መሰንዘር የምትፈልጉ በኢሜል አድራሻችን ላኩልን፡፡

♣ ♣ ♣

ኢሜል፡ fss@ethionet.et

## መግቢያ

በአርብቶ አደርነት በኢትዮጵያ ቆላማና ከፊል-ቆላማ አካባቢዎች በተለይም በደቡብና በምሥራቅ የሀገሪቱ ጠረፍ አካባቢዎች የሚገኝ የኑሮ ዘይቤ ነው፡፡ በጂኦግራፊያዊ እና በጊዜ ተለዋዋጭ የሆነውን አካባቢውን የተፈጥሮ ሀብቶችበሚገባ ለመጠቀም ሲሉ አርብቶ አደሮች በስትራቴጂካዊ በሆነ ሁኔታ ከቦታ ወደ ቦታ በመንቀሳቀስ ኑሯቸውን ይመራሉ፡፡ አነስተኛ የህዝብ ብዛትና ስርጭት የአርብቶ አደር አካባቢዎች አንዱ ዋና መገለጫ ሲሆን፣ አርብቶ አደሮቹም የአካባቢዎቹን የአየር ንብረትና ተያያዥ ችግሮችን መቋቋም የሚችሉ ከብቶች ዝርያዎች ማርባት ላይ ትኩረት ያደርጋሉ፡፡

## በአርብቶ አደርነት በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ አርብቶ አደሮች ከጠቅላላው ህዝብ ቁጥር 15% ያህል ሲሆኑ ከአገሪቱ ጠቅላላ የመሬት ሽፋን ከግማሽ በላይ የሚሆነውን ክፍል ይሸፍናሉ፡፡ የአገሪቱ አንድ ሦስተኛው የቀንድ ከብቶችና በጎች፣ 70 በመቶ የሚሆኑት ፍየሎች እና ሁሉም ግመሎች የሚገኙትም በዚሁ የአርብቶ አደሮች የምርት ስርዓት ውስጥ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ወደውጭ አገር ከምትልከው የቁም ከብት መካከል 90 ከመቶ የሚሆነው (ከአገሪቱ ጠቅላላ የኤክስፖርት ሸቀጥ መካከል አንድ አምስተኛ የሚሆነው) ከአርብቶ አደር የምርት ስርዓት የሚመጣ ነው፡፡ በተጨማሪም አርብቶ አደሮች ከአገሪቱ ዓመታዊ የወተት አቅርቦት ውስጥ አራት አምስተኛውን ይሸፍናሉ፡፡ ይሁን እንጂ በቆላማዎቹ አካባቢዎች በተደጋጋሚ የሚከሰተው ድርቅ እና ተያያዥ የምግብ ዋስትና ችግሮች ይህንን የአርብቶ አደር ምርት ስርዓት ምርታማነት ጎልቶ እንዳይታይ አድርጓል፡፡

## አርብቶ አደር እና መሬት

በኢትዮጵያ በተከታታይ ወደስልጣን የመጡት መንግስታት ስለ አርብቶ አደርነትያላቸውንአመለካከት እና የሚወስኗቸው ውሳኔዎች ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ሦስት ዋና ዋና ቁም ነገሮች አሉ፡፡እነርሱም 1ኛ) የአርብቶ አደሩ የምርት ስርዓት ‹‹ከመንግስት›› ባህል ጋር አለመጣጣም እና አርብቶ አደርነትን በተመለከተ ስር የሰደዱ አሉታዊ አመለካከቶች ለዘመናት መስፈን፣2ኛ) የአካባቢዎቹ የተፈጥሮ ሀብት ስጦታዎች እና (3) የአርብቶ አደር አካባቢ መሬቶችን የካፒታሊዝም የማምረቻ ስርዓትን በመጠቀም ወደ ሌላ “ምክንያታዊ” አጠቃቀም የመለወጥ ፍላጎት ናቸው፡፡

በመጀመሪያ፣ የኢትዮጵያ ‹‹መንግሥት ባህል›› በደጋማ አካባቢዎች በሬን ተጠቅሞ ማረስ ላይ ያተኮረ በመሆኑ የአርብቶ አደር የኑሮ ዘይቤ (በተለይም ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ) እንደ ‹ኋላቀርነት› ምልክት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በተራው ህዝብና በመንግስት ዐይን አርብቶ አደርነት ሰፋፊ ቦታዎችን የሚያባክን እና ምርታማነቱ አነስተኛ የሆነ የምርት ስርዓት ተደርጎ ይታያል፡፡ በዚህም ሳቢያ በአጠቃላይ አርብቶ አደርነት እንደ ‹‹የወደፊት ተስፋ የሌለው›› በሌላ መተካት ያለበት ‹የኑሮ ስርዓት›፣ አርብቶ አደሩ ህዝብም ከዚህ ‹‹ተስፋ ቢስ›› ስርዓት ታድጎ መልማት የሚያስፈልገው ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ በተጨማሪም አርብቶ

አደሮችን እንደ ‹‹ጠበኛና ግጭት ናፋቂዎች›› አድርጎ መመልከትም የተለመደ ነው::አርብቶ አደሮች ከመንግስት፣ ከኢንቨስተሮችና እርስ በርሳቸው በግጭት የተሞላ ግንኙነት እንዲያዳብሩ ያደረጓቸው ምክንያቶች በሚገባ ባለመመርመራቸው ውጤታማ የግጭት መፍታ ዘዴ መቀየስና መተግበር አልተቻለም::ይልቁንም በብሔረሰብ/ቋንቋ ላይ በተመሰረተው የክልል አደረጃጀት እና በዚሁ ሳቢያ የተፈጠረው አንድን አካባቢ የኔ ብቻ ነው የሚል ‹‹የብቸኛ ባለቤትነት ስሜት›› መዳበር፣ ሕገ-ወጥ የኮንትሮባንድ ንግድና ሕገ-ወጥ የሰዎች ማዘዋወር ኔትወርክ እና ሌሎች ተያያዥ ምክንያቶች በአርብቶ አደር አካባቢዎች የሚተዋሉትን ግጭቶች ይበልጥ አወሳስበውታል::

በሁለተኛ ደረጃ፣ በቆላማዎቹ አርብቶ አደር አካባቢዎች ያሉት የተፈጥሮ ሀብት ስጦታዎች (ማለትም ለሰፋፊ ሜካናይዝድ እርሻ ምቹ የሆነ መሬት፣ ዝቅተኛ የህዝብ ብዛት እና ለመስኖ እርሻ ተስማሚ ወንዞች) አካባቢዎቹን ለሰፋፊ የንግድ እርሻዎች ተስማሚ አድርገዋቸዋል:: አብዛኛው ውሀ-ገብ ያልሆነው የአርብቶ አደር ቆላማ መሬት ደረቅ እና ለመስኖ እርሻ የማይመች በመሆኑ መንግስት አርብቶ አደሮቹ በበጋ ወቅት ለግጦሽ እንዲሁም በክረምት ለደለል እርሻ የሚጠቀሙባቸው ቁልፍ መሬቶች ለሰፋፊ እርሻ ለመጠቀም ይሻል:: በዚህ የመንግስት ምኞትና እርምጃ ሳቢያ የአርብቶ አደሩ የአኗኗር ዘይቤ ከባድ ተፅዕኖ ደርሶበታል::

ይህ ሂደት ኢትዮጵያ ባለፉት አስራ አምስት ዓመታት ባካሄደቻቸው ቁጥራቸው የበዛ የሀይድሮ ኤሌክትሪክ ግድቦች ግንባታ ሳቢያ ተባብሷል:: ግድቦቹ በአካባቢዎቹ የሚፈሱት ወንዞች የውሀ ፍሰት በመቆጣጠር ለደለል እርሻና የበጋ ወቅት ግጦሽ ያገለግል የነበረውን የክረምት ወቅት የውሀ ሙላት ከማስቀረታቸው በላይ መሬቱን የመስኖ እርሻ አመቺ ያደርጋሉ:: ይህ በቆላማ አካባቢዎች ሰፋፊ እርሻዎችን የማስፋፋት ስራ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሞከረው ከ1960ዎቹ አካባቢ በአዋሽ ሸለቆ ውስጥ ሲሆን፤ ከ2010 መጀመሪያ ጀምሮ ደግሞ በኦሞ ሸለቆ ተጠናክሮ ቀጥሏል:: በዚህ ሁኔታ አርብቶ አደሮች የሚገለገሉባቸው ቁልፍ የተፈጥሮ ሀብቶች እየተወሰዱ በሌላ የመሬት አጠቃቀም ስርዓት ውስጥ እንዲገቡ ተደርጓል::

ሦስተኛ፣ የአርብቶ አደሩ ሥርዓት ከሚፈጥረው ዕሴት እና በውስጡ ከተከማቸው ሀብት ጋር ሲወዳደር መተዳደሪያ-ተኮር (subsistence-oriented)በመሆኑ በቀጥተኛ ገቢ ደረጃ ለመንግስት የሚያበረክተው ጥቅም ውስን ነው:: በመሆኑም በተከታታይ ወደ ስልጣን የመጡ መንግስታት የሰፋፊ እርሻ ልማትን ከማበረታታቸው በተጨማሪ አርብቶ አደሮች በአንድ አካባቢ በመንደር ተሰባስበው እንዲኖሩና የእንስሳት እርባታ ስርዓቱም ወደ ንግድ ስርዓት እንዲገባ ሲጥሩ ኖረዋል:: አርብቶ አደሮች በመንደር ተሰባስበው እንዲሰፈሩ ማድረግና የእንስሳት እርባታ ስርዓቱን ወደ ንግድ የማስገባቱ ጥረት ሀብታም የአርብቶ አደሮችንየጠቀመ ድሀዎችን ግን የጎዳ የግጦሽ መሬቶች መበጣጠስን አስከትሏል::

## የአየር ንብረት ለውጥ እና ወረራ ያላቸው ዝርያዎች

የአርብቶ አደር የግጦሽ መሬቶች ምርታማነት ማሽቆልቆል በምርት ስርዓቱ ላይ ከፍተኛ አንድምታ እንደሚኖረው ይታወቃል:: እነዚህን የግጦሽ መሬቶች ወደ ግል ይዞታና ወደ ሰፋፊ እርሻዎች በሚለወጡበት ጊዜ ወራሪ ተክሎች/ዕፅዋት ዝርያዎች በቀላሉ ወደ ቀሪዎቹ አርብቶ አደሮች መሬቶች ይስፋፋሉ::የአርብቶ አደሮች ከብቶች በቀረው አነስተኛ መሬት መከማቸት በሂደት የግጦሽ መሬቶቹን ስፋትና ጥራት በመቀነስ ምርታማነት ያሳንሳል:: በዚህ ላይ የአየር ንብረት ለውጥ በአርብቶ አደሩ የምርት ስርዓት ላይ ተጨማሪ ጫና ያስከትላል::

የአርብቶ አደር የምርት ስርዓት በተገደበ የመኖ አቅርቦት ለዘወትር ሊዘልቅ እንደማይችል ይታወቃል:: በመሆኑም፣ የመኖ አቅርቦት መፍትሔ ካልተሰጠው ስርዓቱ ሊቀጥል የማይችልበት ደረጃ ላይ መድረሱ አይቀሬ ነው:: በፈጣን ሁኔታ በመስፋፋት ላይ የሚገኙት ሰፋፊ እርሻዎች፣ አርብቶ አደሮች በመንደር እንዲሰባሰቡ የሚደረገው ግፊትና የወል የሆነው የአርብቶ አደሮች የግጦሽ መሬቶች ወደ ግል ይዞታ የማዛዉ ሂደት ስርዓቱን ሊቀጥል ወደማይችልበት ደረጃ እያቃረቡት ይገኛሉ::

## የከተሞች መስፋፋት እና የዘመናዊው ኢኮኖሚ

በአሁኑ ጊዜ እንደሚታየው አርብቶ አደሮች በእጃቸው ያለው ነገር ግን እያሽቆለቆለና እየተመናመነ በመጣው የተፈጥሮ ሀብት ዘላቂ ኑሮ ለመምራት ይችላሉ ብሎ ማሰብ አዳጋች ነው::ይህ ሂደት እየተስፋፋ በመጣው የመሠረተ-ልማት እና በከተሞች ዕድገት አማካይነት ምናልባትም አርብቶ አደሮችን ወደ ዘመናዊው ኢኮኖሚ እንዲቀላቀሉ ሊገፋፋቸው ይችላል:: የዚህ ዓይነት ጣልቃ ገብነቶች የሚያስከትሉት የአጭር ጊዜ አሉታዊ ውጤት ከፍተኛ ቢሆንም፣ትምህርትና ጤና በመሳሰሉ የተመጣጡ አገልግሎቶች

ከተደገፈ ዘመናዊው ኢኮኖሚ አያሌ ዕድሎችን ሊያበረክት ይችላል፡፡ ከአርብቶ አደር ስርዓት ተገፍተው ለሚወጡት የስራ ዕድሎችን መፍጠርና በስርዓቱ ውስጥ ላሉት ደግሞ ለሚደርሱባቸው የተለያዩ ተግዳሮቶች የተሻሉ የመቋቋሚ መንገዶችን መስጠት ከነዚህ ዕድሎች መካከል ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

የፖሊሲ ምክረ-ሀሳቦች

በዚህ ጽሁፍ አርብቶ አደሮች እያጋጠሟቸው ያሉትን መሠረታዊ የአካባቢ ጥበቃ እና ፖሊሲ ነክ ችግሮች ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ በዓመታት ውስጥ የተተገበሩ መልካም ያልሆኑ ፖሊሲዎችና ‹‹የልማት›› ጣልቃ ገብነቶች በቆላማ አካባቢዎች ያሉትን እምብዛም አመቺ ያልሆኑ የተፈጥሮ ሀብቶችን በብቃት የሚጠቀመውን የአርብቶ አደር የኑሮ ስርዓት (pastoral production system) ዘላቂነት አጠያያቂ አድርገውታል፡፡የአርብቶ አደር አካባቢዎችን ችግሮ ለመቅረፍ ቀደም ሲል ተሞክረው ውጤት ያላመጡትን ‹‹መፍትሔዎች›› ዛሬም እንደገና መሞከርና ውጤት መጠበቅ የዋህነት ይሆናል፡፡ በመሆኑም የአርብቶ አደሮችን የኑሮ ሁኔታ በአዎንታዊ መልኩ ለመለወጥና የኑሮ ዘይቤውን ዘላቂነት ለማረጋገጥ በአዲስ አመለካከት ላይ የተመሰረተ አዲስ መፍትሔ መፈለግ ይገባል፡፡ ለዚህም ይረዳ ዘንድ የሚከተሉት ምክረ-ሀሳቦች ተሰንዝረዋል፡፡

1. አሳታፊ የአርብቶ አደር ልማት ፖሊሲ መቅረጽ፡-ከዚህ ቀደም የአርብቶ አደር አካባቢ ልማት ዕሳቤዎችና ትግበራዎች በልሂቃን የሚቀረፁና የሚታቀዱ፤ እንዲሁም በይዘታቸው የአርብቶ አደር የኑሮ ዘይቤ የመጨረሻው የዕድገት ደረጃውላይ የደረሰና ዕጣ ፈንታውም መለወጥ ነው በሚል አመለካከት ላይ የተመሠረቱ ነበሩ፡፡ ዕሳቤውበራሱ የባህል አድልዎ (biase) ያለበት ሲሆን ይህም አርሶ አደሩን በመንደር ማሰባሰብና የሰፋፊ እርሻዎች ልማት በመሳሰሉ ፖሊሲዎች ላይ ይንጸባረቃል፡፡ በመሆኑም ይህን ስር የሰደደ የተሳሳተ አካሄድ ለመቀየር የመጀመሪያው እርምጃ መሆን የሚገባው በፖሊሲ ማርቀቁ ስራ ላይ አርብቶ አደሮቹንና እውነተኛ ተወካዮቻቸውን በፖሊሲ አወጣጥ ሂደት ውስጥ ማሳተፍ ይሆናል፡፡ ይህ አካሄድ ፖሊሲ አውጪዎች ለአርብቶ አደሮች ሳይሆን ከአርብቶ አደሮችጋር ፖሊሲ እንዲያወጡ ይረዳቸዋል፡፡

2. የአርብቶ አደር አካባቢ የግጦሽ መሬቶችን ጥራት መጠበቅ፤ መጠኑ እንዳይቀንስ ማድረግ፡-በአርብቶ አደሮች አካባቢዎች ከወራሪ ተክሎች እስከ የአየር ንብረት ለውጥ፤ የወንዞች ፍሰቶችን ከመገደብ እስከ የግጦሽ መሬቶችን ወደ ግል ሰፋፊ እርሻ መሬቶች መቀየር በመሳሰሉ ምክንያቶች የአርብቶ አደሮች የግጦሽ መሬት መጠንና ምርታማነት እየቀነሰ መጥቷል፡፡ መሬት ለአርብቶ አደር የምርት ስርዓት ያለውን ቁልፍ ስፍራ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ይህ አይነቱ አሉታዊ ለውጥ በአርብቶ አደሩ ኑሮና በምርት ሥርዓቱ ላይ የሚያስከትለው ከፍተኛ ችግር ልብ ሊባል ይገባል፡፡ ስለሆነም መንግስት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የግጦሽ መሬቶች ማልማት እንዲሁም የሰፋፊ እርሻ ልማቶች በአርብቶ አደር አካባቢዎች በዘፈቀደ ከመስፋፋት እዲቆጠቡ በተገቢውንሁኔታ መቀየስ ይኖርባቸዋል፡፡የወራሪ ተክሎችን መስፋፋት የመቆጣጠሪያ ዘዴዎችም ሊበጁ ይገባል፡፡

3. የተሻለ የግጭት አፈታት መንገዶችን መቀየስ፡-አብዛኛዎቹ የአርብቶ አደር ድንበሮች ከመንግስት ጥብቅ ቁጥጥር ውጭ ሆነው ይታያሉ፡፡በመሆኑም መንግስት በነዚህ ቆላማ አርብቶ አደር አካባቢዎች ህግና ስርዓትን በተገቢው ሁኔታ ለማስፈን ሲያዳግተው ይስተዋላል፡፡ ስለሆነም አርብቶ አደር አካባቢዎች የሚከሰቱ ግጭቶችን ለመከላከል እና ለመፍታት መንግስት ከማህበረሰቦቹ ባህላዊ መሪዎችና ሽማግሌዎችጋር በትብር መስራት ይኖርበታል፡፡

4. በአርብቶ አደር አካባቢዎች የሚሰጡትን ማህበራዊ አገልግሎቶች ተደራሽነት፣ ጥራትና መጠን ማሻሻል፡- ትምህርት ቤት እና የጤና ተቋማትን ጨምሮ በአርብቶ አደር አካባቢዎች ያለው የዘመናዊ ማህበራዊ አገልግሎቶች ተደራሽነት ደካማ ነው፡፡ ይህ ወጣቱ ወደ ዘመናዊው ዘርፍ በመቀላቀል አርብቶ አደርምርት ስርዓት ላይ ያለውን ጥገኝነት የመቀነስ ዕድል ያጠብበዋል፡፡ ስለሆነም የአርብቶ አደር የምርት ስርዓትን ዘላቂነት ለማረጋገጥ እንዲቻል የትምህርት አገልግሎት የሚሻሻልበትን ዘዴ መዘርጋት አስፈላጊ ነው፡፡



በፋና ገብረሰንበት (ዶ/ር)

ምንጭ፡ ፋና ገብረሰንበት (2013) አርብቶ አደርነት የመሬት አጠቃቀምና መብት በኢትዮጵያ


ምስጋናና ማሳሰቢያ

ይህ የፖሊሲ ፍሬ ሀሳብ የታተመው የኦፕን ሶሳይቲ ኢኒሼቲቭ ፎር ኢስተርን አፍሪካ (Open Society Initiative for Eastern Africa) የገንዘብ ድጋፍ ነው በዚህ ህትመት ውስጥ የተገለጹት አስተያየቶች የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የሥራ አመራር ቦርዱን፣የድርጅቱን አጋሮችና የገንዘብ ድጋፍ የሠጠውን የኦፕን ሶሳይቲ ኢኒሼቲቭ ፎር ኢስተርን አፍሪካ (Open Society Initiative for Eastern Africa) አቋምና አመለካከት ላያንጸባርቅ ይችላል::



§§ አድራሻ፡- ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ (FSS) §§ ፖ.ሣ.ቁ.፡- 25864 ኮድ 1000 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

§§ ስልክ፡- 011154 56 05/06 §§ ፋክስ፡- 011154 56 07 §§ ኢሜል፡- fss@ethionet.et §§ ድረ-ገጽ፡- www.fssethiopia.org